የሰ/መ/ቁ. 40229

ታህሳስ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ኸይሮ መሐመድ - ጠበቃ አታክልት ሃ/ስላሴ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ መዲና በያን - ቀረቡ

2. አቶ ደኑር አብደላ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ሲሆን የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ በአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከተወሰነ በኋላ የንብረት ክፍፍሉንም ፍ/ቤቱ ተመልክቶ በ8-2-2000 ዓ.ም ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ የእኔን ሚስትነት ሰርዘው እኔ በማላውቀው ሁኔታ የባልና ሚስት ፍቺ አስወስነው የንብረት ክፍፍልም እንዲደረግ የተወሰነ ስለሆነ ይህ ውሳኔ የእኔን መብት የሚጐዳ ስለሆነ ይሰረዝልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የመቃወም አመልካች በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር በቀጠሮ ላይ እንዳለ ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የጣልቃገብነት አቤቱታ አቅርባ አመልካችና ተጠሪ (የአሁን ተጠሪዎች) መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነገር ግን የመቃወም አመልካች ትዕዛዙን ባለማድረሳቸው ድጋሚ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በድጋሚውም ትዕዛዝ መሠረት ባለመፈጸማቸው አቤቱታቸውን ባለመቀበል ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው ደግሞ ክርክር እየተደረገ መሆኑን ያልተገነዘበ ወገን በሌለበት ክርክር ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ መብቱን የነካበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ነገር ግን ክርክር መኖሩን የተገነዘበ ሰው ከበስተጀርባ ሆኖ የክርክሩን ሚዛን በመገምገም እርሱን በሚመለከት አጥጋቢ ፍርድ ባልተሰጠ ጊዜ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ማቅረብ ከሥነ-ሥርዓት ሕጉ ዓላማ አኳያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በዚህም ጉዳይ የመቃወም አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ለመሆን አቤቱታ አቅርባ መጥሪያ እንድታደርስ ለሁለት ጊዜ ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም በትዕዛዙ መሠረት ሳትፈጽም ቀርታ ከውሳኔ በኋላ ወደ ክርክሩ ለመግባት አቤቱታ ማቅረቧ ክርክር መኖሩን እያወቀች ስለሆነ አቤቱታው በተገቢው አኳኋን አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ መ/ሰጭዎችን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተገቢነቱን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማንኛውም ሰው ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ለማቅረብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 ላይ ተመልክቷል፡፡

መቃወሚያ ማቅረብ የሚፈቀድበት ደንብ መሠረታዊ ዓላማም ምንአልባት ፍርድ መስጠቱን ያላወቀና በተሰጠው ፍርድም ጥቅሙ የሚነካ ሰው ፍርዱ ቢፈጸም በጥቅሙ ላይ ሊከተል የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል ነው፡፡ አንድ ሰው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ለማቅረብ የሚችለውም በጉዳዩ የሚያገባውና በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 41 መሠረት የክርክሩ ተሳታፊ ሊሆን የሚችል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ነው፡፡ አመልካችም በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር ስለሚመለከተኝ የክርክሩ ተሳታፊ መሆን ይገባኛል ብለው በፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 41 መሠረት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ነበር፡፡ አቤቱታቸውም ተቀባይነት አግኝቶ ፍ/ቤቱ ክርክሩን አግዶ የጣልቃገብነት ማመልከቻው ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስና መልስ እንዲሰጡበት ከአንድም ሁለት ጊዜ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የጣልቃገብነት አቤቱታ ለተከራካሪ ወገኖች ሳይደርስ የቀረው በአመልካቹ ጉድለት በሆነ ጊዜ ደግሞ ጣልቃገቡ ነገሩን ሆነ ብሎ እንደተወው ተቆጥሮ መብቱ እንደሚሰረዝበት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 41(4) ላይ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች በተጠሪዎች መካከል ክርክር እየተደረገ መሆኑን ተገንዝበው በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቀው ተፈቅዶላቸው የጣልቃገብነት አቤቱታውን ለተከራካሪ ወገኖች ማድረስ ሲገባቸው ይህን ሳይፈጽሙ ቀርተው መብታቸው ከተሰረዘ በኋላ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ ማቅረባቸው ክርክር መኖሩን በሚገባ በተገነዘቡበት ሁኔታ ስለሆነ በዚህ መልኩ የሚቀርብ አቤቱታ ከሕጉ ዓላማ ጋር ስለማይጣጣም የሥር ፍ/ቤቶች አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ እንጂ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## **ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 56832 በ20/8/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 67878 በ21/11/2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ